# የግንቦት 7 ድምጽ

አንብበው ያስነብቡ ! አባዝተው ያሰራጩ !

የግንቦት 7 ቿፍትሕ፣የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ሳምንታዊ ልሳን፤

www.ginbot7.org

ቁጥር 20 መስከረም 22 2001 ዓ.ም


# የመለስ ዜናዊ የኢኮኖሚ እድገት ቅጥፈት በባለሙያተኞች ተጋለጠ።

## “መቼ ጨኽኩና !” አለ አባ ውዴ

ከኢኮኖሚ ጉዳይ ዘጋቢያችን አዲስ አበባ

ድሮ ሕጻን እያለን አባ ውዴ (ላሊበላ) ወትሮ እንደሚያደርገው ሁሉ የመኸር ወቅት ጠብቆ በቀያችን በመዝለቅ ገና ሰማይና ምድሩ ሳይለቀቅ የሰፈሩን የጸጥታ ድባብ በጩኸት ያደፈርሰዋል። በመኸር ሥራ ሲማስን ከርሞ ረጅም እንቅልፍ በቅጡ በማጣጣም ላይ የነበረው ጎልማሳም “አባ ውዴ! በል ይበቃሃል አትጩህ” ሲለው ላሊበላውም መልሶ “ኧረ ጌታው ! ገና መቼ ጨኽኩና” በማለት ለቀጣይ እንጉርጉሮው እንድንዘጋጅ ቁርጡን ነገረን።

ይህን ቀልድ መሰል ዕውነታ ያስታወሰን ሰሞኑን በመካሄድ ላይ በነበረው የኢህአዴግ ሰባተኛ ጉባዔ ጠቅላይ ሚንስትሩ በፕሮፓጋንዳው መስክ ኢህአዴግ ደካማ እንደነበረ በማውሳት ከአሁን በኋላ ግን አምርሮ እንደሚጮህ ለህዝቡ የነገሩት መርዶ ነው።

አባ ውዴ እንኳ ኮሳሳውን አንበሳ፣ ቦቅቧቃውን ጀግና፣ ፋንጋዋን ልዕልት በማለት የሚሸልመው የዕለት ጉርሱን ለማግኘት ሲል ነው፤ ከያኒው እንዳለው ለትንሿ ኑሮ በትልቁ ዜማ! ፋንጋዋ፣ ራሱ አባ ውዴ ዘግኖ “በሰጣት” ውበት ተፍለቅልቃ በሜኖ እህል ስትሰፍርለት ቆንጆ አለመሆኗን አጥታው አይደለም፤ ክፋት የለውምና በአዝናኝነቱ ያልፋል። ለማይጠረቃ የስልጣንና የሀብት ጥማቱ ሲል ኢህአዴግ ምርጫን አጭበርብሮ፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎችን አስሮ፣ በመቶዎች ገድሎ፣ የግል ጋዜጦችን ዘግቶ “እንከን የለሽ ዴሞክራሲ አመጣሁ” የማለት ቀልድ፤ የምግብ እህል ዋጋ ጣሪያ ነክቶና በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች በእህል ምርት እጥረት በሞት አፋፍ ላይ በሚገኙበት ወቅት ሀገሪቷ በግብርና ምርት የመጥለቅለቅ ተረት ተረት፤ ይባስ ብሎም ውሸት ሲታሽ ቢውል የእህል ምርት ላይወጣው ያለፈው የፕሮፓጋንዳ ነጋሪት የህዝብን ጆሮ እንዳልሰቀጠጠ ሁሉ የአሁኑ “የመቼ ጨኽኩና !” ምጸት ግን እንደዋዛ በቀልድነቱ ፈገግ አስደርጎ የሚያልፍ አይደለም፤ ከዚህ መረን የለቀቀ ቅጥፈት ጀርባ የሀገርና የእልፍ አእላፋት ዜጎቿ ህይወት የወደፊት እጣ ፋንታ አለና።

የኢህአዴጉ ቁንጮ ዲስኩራቸውን ሲሰጡ ለወትሮው በዋቢነት የሚጠቅሷቸው የዓለም ባንክና የዓለም የገንዘብ ድርጅት አልነበሩም። የዓለም ባንክ ወደህሊናው ተመልሶ አመጣነው ያሉትን እድገት የተጠራጠረ ሲመስላቸው ፊታቸውን ወደሌላ የአይጥ ምስክር አዙረዋል፤የቻይና ኮምዩኒስት ፓርቲና ሰሜን ኮሪያ! ሁለት ባላ ትከል፣ አንደኛው ሲሰበር ወደአንዱ ተንጠልጠል መሆኑ ነው። አንድ ራሱን መቻል ያቃተው ነፍስ ለማትረፍ ሚሊዮን ነፍሶችን መቅጠፍና ለሁሉም ነገር መፍትሄው “አንድና አንድ ብቻ” መሆኑን ወዳስተማረን ሶሻሊዝም እያመራን እንዳይሆን ያሰጋል።

ጆርጅ ኦርዌል በ1948 በጻፈውና 1984 ብሎ በሰየመው መጽሀፉ ውስጥ በትንበያ መልክ ቁልጭ አድርጎ ያስቀመጣቸው ጉዶች እነዚህና መሰሎቻቸው መሆን አለባቸው። ስለሚነገረው ግን ስለማይታየው የኮምዩኒስቶች የኢኮኖሚ እድገት ጆርጅ ኦርዌል በምጸት ሲገልጽ፤ “...እንደተለመደው በአገዛዙ ቁጥጥር ስር ያለው የሬዲዮ ጣቢያ ስለተለያዩ የእርሻና የኢንዱስትሪ ምርቶች ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በከፍተኛ አሃዝ ማደጋቸውን ከአበሰረ በኋላ፣ በተገላቢጦሹ ደግሞ የነፍስ ወከፍ የስንዴ ሬሽን ከ50 ኪግ ወደ 25 ኪግ መቀነሱን በመግለጽ የእለቱን ስርጭት ያጠናቅቃል። በሚቀጥለው ቀን ደግሞ ይሄው ቀልደኛ ሬዲዮ ምርት በከፍተኛ ሁኔታ በማደጉ ምክንያት የስንዴ ሬሽን ወደ 25 ኪግ ማደጉን ይገልጻል። ትላንትና እኮ 50 ኪግ ነበር ብሎ ማን ወንድ ነው የሚጠይቀው !? ነገር ይመጣላ !” በማለት ተሳልቋል።

መቼም የኢህአዴግ የውሸት ቱልቱላ ያልዳሰሰው መስክ የለም። የህዝቡን በነጻነትና ዴሞክራሲ እጦት መሸማቀቅና በፍጹም አፈና ሥር መሆንን፣ በሀገሪቱ ውስጥ በተፈጠረ የምግብ እህል እጦት የተራቡ ወገኖቻችን የሰቆቃ መጠንና ከጥቂት የሥርዓቱ ባለሟሎች ውጪ ያለው ብዙሃን በኑሮ ውድነት ህልውናው በእጅጉ እየተፈተነ መሆኑን፣ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የሚነሱ አስፈሪ ግጭቶችን ወዘተ በመተንተን ገዥዎቹ አመጣንልህ የሚሉትን ዴሞክራሲ፣ ኢኮኖሚያዊ እድገት፣ እንዲሁም ሰላም ፍጹም ሀሰትነት ለህዝብ ለማስረዳት መሞከር ጊዜ ማባከን ሊሆን ይችላል፤ እውነታውን የችግሩ ገፈት ቀማሽ የሆነው ራሱ ህዝቡ ያውቀዋልና ! ይልቁንስ አቅም ያለው ዜጋ መፍትሄ ሊሆን በሚችል ጉዳይ ላይ ቢያተኩር ለሚፈለገው ለውጥ መፋጠን የተሻለ አስተዋጽዖ ይኖረዋል። ነገር ግን ውሸት ሲደጋገም ዕውነት ይመስላል እንዲሉ አንዳድ ብዥታዎችን ለመከላት ያህል ቢያንስ ሙያዊ መነጽር በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ ውሸቶቹንና ተቃርኖዎቹን መጠቆም ተገቢ ይሆናል። የተደገሰውንም የኢህአዴግ ልፈፋ በትዝብት ብቻ ማለፍ የወገንንና የሙያን ሞራላዊ ግደታ አለመወጣት ይሆናል።

ሀሳቡ ከተነሳ አይቀር ከብዙ ውጥንቅጥ የበዛባቸው የኢህአዴግ የስኬት የፋከራ መስኮች መካከል ስለኢትዮጵያ የግብርና ምርትና አጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገት ጥቂት ካልን በኋላ፤ በዋጋ ንረትና በገንዘብ አቅርቦት መካከል ያለውን ትስስር በማሳዬት ይችን አጭር መጣጥፍ እናሳርጋለን።

በአለፉት ሁለትና ሶስት አመታት ተገኝቷል ስለተባለው የኢኖኖሚ እድገት በተቃራኒው ደግሞ ስለተከሰተው የዋጋ ግሽበት ብዙ መላ ምቶች ሲሰጡ ቆይተዋል። አሁን ደግሞ በአብዛኛው የአገሪቱ ክፍሎች ህጻናት በረሃብ ምክንያት በሞት እየተነጠቁ በማየት ላይ እንገኛለን። እነዚህን እርስ በእርስ የሚጋጩ ኩነቶችን ስናይ ኢህአዴግ የነገረንን የእርሻ ምርት እድገት በሚታየውና በሚዳሰሰው ኑሯችን ብቻ ሳይሆን አሸተው ያቀረቡልን መረጃ እስካፈናፈነ ድረስ በሙያ መነጸርም ለመፈተሽ ግድ ይለናል። ሊደበቁ ከማይችሉት ክስተቶች በመነሳት ለቀረበው ጥያቄ መልስ ለመስጠት በኢኮኖሚክስ የጠለቀ እውቀት የሚያስፈልገው አይመስልም። ለዚህም አብይ ምክንያቱ እንደ ኢትዮጵያ ባለ ግብርና መር በሆነ ኢኮኖሚ ውስጥ ትልቁ የኢኮኖሚ እድገት ይህንን የኢኮኖሚ ክፍል መሰረት ያደረገና በተጨባጭ ምርት የተደገፈ እስከሆነ ድረስ እንደዚህ ያለ ፈር የለቀቀ የእርሻ ውጤቶች የዋጋ ግሽበት ሊከሰት ስለማይችል ነው። ነገር ግን ላለፉት ሶስትና አራት አመታት ተገኝቷል የተባለው እድገት በምርት ያልተደገፈና በመንግስት ወጪ ምክንያት የመጣ (overheating) ከሆነ በእርግጥም ሊገርም አይችልም። የአለም ገንዘብ ድርጅት መንግስት ወጪውን መቀነስ እንዳለበት በማሳሰብ ላይ የሚገኘውም ለዚሁ ነው፤ እንደዚህ አይነቱ እድገቱ ቀጣይነት ስለማይኖረው። ነገር ግን ለኢኮኖሚክስ ትንታኔ ግራ የሚያጋባውና የአለም የገንዘብ ድርጅትም ሊጠይቅ ያልደፈረው ክስተት ኢህአዴግ ያቀረበው መረጃ እድገቱ በአብዛኛው (በአማካይ ከ60 ከመቶ በላይ) የተገኘው ከግብርና እንደሆነ አድርጎ ማሳየቱ ነው። የዓለም የገንዘብ ድርጅት ለማመላከት እንደሞከረው እድገቱ ከፍላጎት ወገን በተለይም በመንግስት ወጪ መናርና ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ኢኮኖሚውን እንዲያጥለቀልቅ በመደረጉ ምክንያት ቢሆን ኖሮ የክርክሩ ነጥብ ሌላ ይሆን ነበር።

ከዚህ አንጻር አገሪቱ ካለችበት ሁኔታ በመነሳት መረጃው ተዓማኒ የማይሆንበት ምክንያት የጎላ ነው። በተለይ ደግሞ በተለያዩ መሥሪያ ቤቶች የሚቀርቡት መረጃዎች ልዩነታቸው በጣም የሰፋ በመሆኑ ለማስታረቅ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ እናያለን። የግብርናውን ክፍለ-ኢኮኖሚ በተመለከተ መረጃ የሚሰበስቡት መሥሪያ ቤቶች የማእከላዊ ስታትስቲክስ ኤጄንሲና የግብርና ሚኒስቴር ናቸው። የማእከላዊ ስታትስቲክስ መረጃ አሰባሰብ ናሙናን መሰረት ያደረገ ሲሆን የግብርና ሚኒስቴር ደግሞ በቀበሌ ደረጃ የሚገኙትን የልማት ሰራተኞች (ዛሬ ዲግሪ አሳዳጅ ተብለው የተፈረጁትን ካድሬዎች) ግምት መሰረት ያደረገ ነው። ከመረጃ ሰብሳቢዎቹ አፈጣጠርና ፍላጎት በመነሳት ሊኖር የሚችለውን የመረጃ ልዩነት መገመት አዳጋች አይሆንም። ካድሬዎቹ በገምጋሚዎቻቸው ፊት ሚዛን የሚሞሉትና በቀጣይ የሚጠብቁት ዳቦ ውፍረት የሚለካው በሥራቸው ያሉት ገበሬዎች በተለይ ከምርት ጋር በተያያዘ በሚያሳዩት ለውጥ ነው። ለአብነት ያህል በግል ገበሬዎች የታረሰውን መሬት በተመለከተ በሁለቱ የመንግስት ድርጅቶች የተሰራጨውን መረጃ ስንመለከት (ሰንጠረዥ አንድን ይመልከቱ) እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1994ና 1995 በግብርና ሚኒስቴርና በማእከላዊ ስታትስቲክስ መካከል ከ40 በመቶ በላይ ልዩነት ነበረ። ይህ ልዩነት ግን ከፍተኛ እድገት ታይቷባቸዋል በተባለባቸው ባለፉት ሶስት አመታት ከ15 በመቶ በታች ሆኖ እናገኘዋለን። በተጨማሪም የታረሰው የመሬት ስፋት በማእካላዊ ስታትስቲክስ ስሌት በ1994ና 1999 መካከል በ35 ከመቶ ማደጉን ያሳያል። ከዚህ የምንረዳው ነገር ቢኖር የታረሰው የመሬት ስፋት እየጨመረ መሄዱን ብቻ ሳይሆን የማእከላዊ ስታትስቲክስ ስሌት ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በፍጥነት እየተቀራረበ መሄዱን ነው። በአንድ በኩል እንዲህ በግማሽ ዓሥርተ ዓመት የታረሰ መሬት ከሣሶ እጅ በላይ መጨመሩ ይህ መሬት ከየት መጣ ያሰኛል። በሌላ በኩል ደግሞ በሁለቱ መሥሪያ ቤቶች የሚሰበሰበው መረጃ መጀመሪያ በእጅጉ መለያየትና በኋላም እየተቀራረበ መምጣት የመረጃውን ተዓማኒ አለመሆን ከማጉላቱም በላይ በስፋት ሲነገር የቆየውን የማእከላዊ ስታትስቲክስ ሠራተኞች መረጃውን እንዲያጣጥሙ (ወይም “እንዲቀቅሉ”) የመገደዳቸውን ዕውነታ ያጠናክራል።

በሌላ በኩል በመረጃው እንደታየው የሚታረስ መሬት ጨምሮ ይህ እድገት ዕውነት እንኳ ቢሆን ኖሮ በኢህአዴግ ፖሊሲ በተለይም በኤክስቴንሽን መርሀ ግብር ያልተገኘ ከመሆኑም በላይ መሬትን ዝንተዓለም እያሰፉ መሄድ ስለማይቻል ቀጣይነት ሊኖረው አይችልም ነበር። ከታች በስዕሉ (ግራፉ) ለማስተዋል እንደሚቻለው ዋና ዋና ሰብሎችን በተመለከተ በኢህአዴግ ዘመን ከደርግ ዘመን የተሻለ ምርታማነት አልታየም። በደርግ ዘመን የነዚህ ሰብሎች ምርት ከአንድ ሄክታር መሬት በአማካይ 11 ኩንታል የነበረ ሲሆን ላለፉት 15 ዓመታት (የመጀመሪያዎቹን የኢህአዴግ ሁለት ዓመታት ትተን) ያው 11 ኩንታል በሄክታር ነበር። ማን ያውቃል፤ ዛሬ ይህን ብለናል፤ ነገ ደግሞ ልክ እንደ አጠቃላይ የሀገር ምርቱ (GDP) ማስተካከያ ተደርጎለት ምርታማነት በወረቀት ላይ ተመንድጎ እናየው፣ በቀጣዩ የኢህአዴግ ጩኸትም እንሰማው ይሆናል !!

ወደ ገጽ 2 ዞሯል

# ርእሰ አንቀጽ

## ፍትህ ስንል ፍትህ ሲሉ

ከግንቦት ሰባት ንቅናቄ ሶስት ምሶሶዎች መሃል አንዱ ፍትህ ነው ። ያለምክንያት አይደለም በምሶሶነት መምረጣችን ። የህግ የበላይነት የተጣሰበት፣ አንድ አምባገነን ህግ እኔ ነኝ ባለበት ሃገር ፍትህ የንቅናቄያችን መሰረት ቢሆን ተገቢ እንጂ ነው ። በተለይ ሰለ ፖለቲካዊ ፍትህ ስናወራ የምናተኩረው የሀገሪቱ ፖለቲካዊና ማህበራዊ መሰረታዊ መዋቅር ስለቆመበት መደላድል ነው ። መለስና ጀሌዎቹ የተገንጣይ ድርጅታቸውን ፕሮግራም ህገ-መንግስት አድርገው ፅፈው በዚያ እንድንተዳደር አቅርበውልን ነበር ። ህዝቡ የመከረበት ፤ የሃገሪቱ ምሁራን የተሳተፉበት፤ የተለያዩ ምናልባትም የሚቃረኑ አስተሳሰቦችና እምነቶች ያላቸው ማህበረሰቦች ተከራክረውበትና ፤ ተጨንቀውበት ፤ የሚስማሙበት የጋራ ድንበር ዘለል (ሁሉን አቀፍ) መፍትሄ ላይ ደርሰው ሃገሪቱን በተደላደለና በተረጋጋ መሰረት ላይ እንዲያቆሙ የወያኔ መንጋ ባለመፍቀዱ የሁላችንን ተስፋ የሚቋጥር ህገመንግስት ማቆም አልተቻለንም ። እብሪተኞቹም ራሳቸው ህገመንግስት ብለው የሰጡን ሰነድ ውስጥ ፤ የምእራብ ለጋሾቻቸውን ለማስታገስ ከእምነታቸው ውጪ ያስገቡአቸው የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ ሃረጎች ስለቆጠቆጡአቸው ፤ የራሳቸውን ህግ ማፍረስ የተገደዱበት ገሃነም ውስጥ እየተቀቀሉ ይገኛሉ ።

እኛ ፍትህ ስንል በእኩልነት የሚያምኑ ሃይሎች በታሪክ በመጣ ጭነትና ዝግንትል ሳይጋረዱ ፤ ሰለመፃኢውም ስርአት ምንነት አስቀድመው ባጡኑትና በወሰኑት ፅንሰ-ሃሳብና ርዕዮተ አለም ሳይታቀቡና ሳይጋረዱ ፤ የተለያዩና ምናልባትም የሚቃረኑ እምነቶችና አስተሳሰቦች እንዲሁም ጥቅሞች ያላቸው ሃይሎች በቀና መንፈስ ሸንጎ ተቀምጠው ፤ "ለልጆቻችን ምን አይነት ሃገር ጥለንላቸው እንሂድ" ብለው መክረው የሚያወጡት የሁሉንም ፍርሃትና ተስፋ ያካተተ ፤ የየትኛውም ቡድን ብቸኛ ተጠቃሚነትና የበላይነት ከሌለበት ፤ የድርድር መድረክ የሚወጣ ሚዛናዊ ሰነድ ነው ። ይህን ከመሰለ ረጅም ድርድር የሚወጣ ሰነድ በመሆኑም ፤ ሁሉም የሚመኘውን በተሟላ መንገድ ማግኘት ባይችልም ፤ መሰረታዊ ፍላጎቱን ግምት ያስገባና ቅን መሆኑን ግን የሚቀበለው ነው የሚሆነው ። ምክንያቱም በዴሞክራሲያዊ መንገድ በመረጣቸው ተወካዮቹ ቀጣይ የሆኑ ማሻሻሎችን ማድረግ እንደሚችል ስለሚያውቅ ነው ።

መለስና ኩባንያው ፍትህ ሲሉ "ከእኛ በላይ ላሳር" የሚል እብሪተኝነት ፥ የፖለቲካ ስልጣኑን በበረሃ ተንከራተን ተንገላተን ያመጣነው ስለሆነ ፤ ፍትህ የዚህ ድካማችን ውጤት የሆነውን እንቁ መጠበቂያ ዘባችን ፥ ስልጣናችንን የሚቀናቀኑትን ማጥቂያ ሰይፋችን ፤ የፖለቲካ አላማችንን መተግበሪያ መሳሪያችን ነው ብሎ ነው የሚያምነው ። ይህ እምነት የሰለጠነው አለም ስለ ፍትህ ካለው ግንዛቤ የተፃረረ የአምባገነኖች ራስ ወዳድና ሃገርን አውዳሚ እምነት ጋር የተጓዳኘ በመሆኑ ፤ ከፍትህነት ሊቆጠር አይገባውም ። በሚያምንበት አመፅ ሊወረወር እንጂ ። ከታሪክ ትቢያ ሊጨመር እንጂ ።

የመለስ ቅጥፈት ከገጽ1 የዞረ

የእህል ምርት ከ1996 እስከ 1999 ባለው የአራት ዓመት ጊዜ ውስጥ ኢህአዴግ እንደነገረን በአማካይ በዓመት በ22 ከመቶ ካደገ፤ የ55 ከመቶ የዋጋ ንረትና ለተራቡ ወገኖቻችን “ከጠላቶቻችን” ሳይቀር ስንዴ መመጽወት ተረት በሆነ ነበር። ከፋቱ እነዚህ የመጥፎ ጊዜ መገለጫዎች በገሃድ የምናያቸው እውነታዎች ናቸው። ይህ ከሆነ ደግሞ፤ ተረት ተረቱ የ22 ከመቶ የግብርና ምርት እድገትና የ11 ከመቶ አጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገት መሆን አለበት። በመሠረቱ በሀገሪቱ የእህል ምርት ዋጋ እንደዚህ ጣሪያ እንዲነካ የእርሻ ምርት የግድ መውረድ አይጠበቅበትም። በኢትዮጵያ ሁኔታ ጥሩ ዝናብ ከኢህአዴግ ፖሊሲ ይሻላልና ተፈጥሮ ፊቷን እስካላዞረች ድረስ በአሥር እንኳ ባይሆን ህዝቡን ለመመገብ የሚያስችል ከሦስት በመቶ ያላነሰ እድገት ሊኖር ይችላል። ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ የዋጋ ንረት ሊያስከትል የሚችለው ግን በግድየለሽነትና በፍጹም ስግብግብነት የተተገበረው የኢህአዴግ የገንዘብና የመንግሥት ወጪ ፖሊሲ ነው። ይሄን ጉዳይ ወደፊት በስፋት የምንመለስበት ይሆናል።

ያለልክ የተንቦረቀቀውን የመንግሥት ወጪ በተመለከተ የጠቅላይ ኦዲተር መሥሪያ ቤት ለፓርላማ ያቀረበውን ሪፖርት መጥቀስ ለጊዜው ይበቃል። ሪፖርቱ እንደሚያሳየው ኢህአዴግ ራሱ ያወጣው ሕግ ከሚፈቅድለት ጣሪያ በላይ 3.3 ቢሊየን ብር በግመጃ ቤት ሠነድ (treasury bills) እና በቀጥታ ብድር ስም ከአገር ውስጥ ባንኮች ወስዶ ኃላፊነት በጎደለው መልኩ መሸከም በማይችለው ኢኮኖሚ ውስጥ ነስንሷል። ይህን ሪፖርት ያቀረቡት የሥራ ኃላፊም “ሁሉን አዋቂ” በሆኑት ጠቅላይ ሚንስትሩና በአደግዳጊዎቻቸው ግልምጫ፣ ዘለፋና፣ ውግዘት ደረሰባቸዋል። በዚህ ጉዳይ ላይ የኢህአዴግን ማስተባበያ ከንቱነት ለመረዳት ዶሴ ማገላበጥን አይጠይቅም፤ ከዚህ ዐይን ገላጭ ሪፖርት በኋላ ከባንኮች የሚበደረውን የገንዘብ መጠን ጣሪያ ከነአካቴው የሚያስቀርና እንዳሻው እንዲዘርፍ የሚያስችለው ሕግ አርቅቆ ለጉድ ለጎለተው የተወካዮች ምክር ቤት ሲያቀርብ አፍታ አልፈጀበትምና። ጆርጅ ኦርዌል ከላይ በጠቀስነው አብይ ሥራው ውስጥ እንሚያስረዳው በእንደነ ኢህአዴግ አይነቶቹ ቤት እውነት ዋጋ የሌላት መናኛ ርካሽ ነገር ናት። የማትቆረጠም ባቄላ ሆና ስትገኝ ትሰረዛለች፣ ትደለዛለች ከነአካቴውም በፈጠራ ተረት ተረት ትቀየራለች። ለአብነት ያህል የግንቦት ሰባቱን ምርጫ ተከትሎ የተከሰተውን ብጥብጥ ለማጣራት የተቋቋመው ኮሚሽን ያቀረበው ሪፖርት እንዴት እንደተቀየረ ማውሳቱ ይበቃል። በተመሳሳይ ሁኔታ የብሔራዊ ባንክ መረጃ እንደሚያሳየው (በሪፖርቱ ላይ የሰፈረውን በጥሬው ስንወስደው) ባለፉት አራት ዓመታት አጠቃላይ የገንዘብ አቅርቦት (broad money) በቀዳሚዎቹ ሰባት ዓመታት ያድግበት ከነበረው የ6 ከመቶ ዓመታዊ ምጣኔ በሦስት እጥፍ አሻቅቦ በ18 ከመቶ አድጓል። ከዚህም ውስጥ ወደኢኮኖሚው በብድር መልክ የገባው መጠን በተመሳሳይ ወቅት በዓመት በ21 ከመቶ የጨመረ ሲሆን በቀዳሚዎቹ ሰባት ዓመታት ግን በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት የነበረውን ከፍተኛ የመንግሥት ብድር ምጣኔ (49 ከመቶ ነበር) ጨምሮ ከ7 በመቶ አይበልጥም ነበር።

ከላይ ያቀረብናቸው ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎች በጥምረት የሚያስረዱት ዋና ጭብጥ የዋጋ ንረቱ የተከሰተው ሌት ተቀን እንደሚለፈፈው በታዬው ተአምራዊ የኢኮኖሚ እድገት ሳይሆን እንደ’ መና ከሰማይ በወረደው የገንዘብ አቅርቦት መሆኑን ነው። ይሉኝታን አርምዶ የበላውና የሀገር መሪ ኃላፊነት ቅንጣት ታክል የማይሰማው ኢህአዴግ ይህን ሲያደርግ፣ በከተሞች ለሚያካሂደው መጠነ-ሰፊ የሀብት ክምችት የዐይኑ ቀለም ለኢህአዴግ የማያምረው ብዙሃን ከተሜ ጫናውን እንዲሸከምለት በማሰብ ነው። ሸፍጠኛውና ቂመኛው ኢህአዴግ የኢኮኖሚ የበላይነቱን ብር እየነሰነሰ ሲያረጋግጥ፤ ከተሜውም በ97ቱ ምርጫ ላወጣት ቀይ ካርድ ወፍራም መቀጫ በኑሮውና በገንዘቡ መክፈል እንዳለበት አምኗል። ግን እስከመቼ መሮጥ እንደሚችል ቆም ብሎ ቢያስብ እንዴት ትልቅ ለውጥ ነበር!

በመጨረሻ አንድ ነገር እንበል። ይቺ አገር ወደማንፈልገውና የሁላችንም መሆን ወደማትችልበት አቅጣጫ እያመራች ለመሆኗ ምልክቶች እየታዩ ነው። የሁላችንም መሆን ሳትችል ስትቀር ደግሞ ሀገር-አልባነት የሚያመጣውን መከራ ለመረዳት የሚሞቱላት ሀገር ኖራ ሺ ጊዜ መሞት መቻል መታደል መሆኑን እንዲያስረዳን ማክሲም ጎርኪን የግድ ከመቃብር መጥራት አይኖርብንም። በእርግጥ ለዚች አገር ደምና አጥንት መክፈል የቻሉ ክቡር ወላጆች አሉን። እነሱ አልተማሩም። የኛ መማር ያስገኘልን እውቀት ከትግል አንጻር በማኪያቶ ዙሪያ ከንቱ ወሬ ከመዘብዘብ ያለፈ ነገር ሊያመጣ ይገባዋል። በእኛ ዘመን ሀገራችንን ለመታደግ የግድ ቋጥኝ መሸከም አይኖርብንም። እልፍ አእላፍ ነንና እንዳቅማችንና እንደሙያችን ጠጠር ካዋጣን ጋሩን መደገፍ እንችላለን። ከዚህ አንጻር የውሸት ፕሮፓጋንዳ በህዝብ ላይ ሲነዛ በተለይ ደግሞ የተዛባ መረጃ ሲቀርብ በተቻለን አማራጭ ሁሉ “ለንቀትህ ለከት ይኑረው!” በማለት በህግ ልንለው ይገባል። ስለዚህ ሁላችንም አቅማችን በፈቀደው መጠን እውነታውን በነጻ ሚዲያዎች አማካኝነት ለህዝብ እንዲደርስ በማድረግ የሙያ ብቻ ሳይሆን የዜግነት ግዴታችንን መወጣት ይኖርብናል። ይህ አይነቱም እንቅስቃሴ የሀገራችንን የሰቆቃ ጊዜ ለማሳጠር አስተዋጽኦ ያበረክታል ብለን ስለምናምን ጎበዝ በያለንበት እንበርታ እንላለን!!

ሰንጠረዥ አንድ፥ የታረሰ የመሬት ስፋት በሺህ ሄክታር

| የተሰበሰበበት አመት | ግብርና ሚኒስቴር | ማእከላዊ ስታትስቲክስ | ክፍልፋይ በመቶኛ (ልዩነት አመልካች) |
|---|---|---|---|
| 1994 | 11347 | 7813 | 145 |
| 1995 | 11018 | 7849 | 140 |
| 1996 | 10304 | 8664 | 119 |
| 1997 | 10640 | 9807 | 108 |
| 1998 | 11417 | 10169 | 112 |
| 1999 | 12148 | 10592 | 115 |

ምንጭ፥ ማእከላዊ ስታትስቲክስ ኤጄንሲና የአለም የምግብ ድርጅት

አማካይ የሰብል ምርት በኩንታል በአንድ ሄክታር ማሳ ላይ
ምንጭ፥ ማእከላዊ ስታትስቲክስ ኤጄንሲና የአለም የምግብ ድርጅት






**የፖስታ ሳጥን ቁጥር ፥** POBox: 4916
2003EX Haarlem
The Netherlands

ሃይለ ሀሳብ

በዚህ አምድ ስር የተለያዩ ነጻነትንና ትግልን የተመለከቱ ጉዳዮች ይስተናገዳሉ

# የግንቦት ሰባት ድምጽ ራዴዮ፣ከአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ጋር ካደረገው ቃለ ምልልስ የተወሰደ ሁለተኛው ክፍል

ጋዜጠኛ
ህዝብ የስልጣንባለቤት እንዲሆን የነጻ ተቋማት ጥያቄ ጉዳይ የማየጠያይቅ ሆኗል። የመለስም አገዛዝ ተቋማቶቹ ነጻ ናቸው ይላልን እንጂ አያስፈልጉም አይልም። ይህ ግልጽ ነው ቀደም ብለው የተጠቀሱት የአንድ ወይም የሁለት አመት አድሜ የሚኖረው ሁሉን ያሳተፈ አላማው የተባሉትን ነጻ ተቋማት መገንባት የሆነ የሽግግር መንግስት በኢትዮጵያ እንዴት እውን ይሆናል። ከአገዛዙ የሚነሳውን ተቃውሞ ትቼ የማተኩረው በተቃዋሚ ፓርቲዎች ላይ ነው። ይህንን የምለው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከአገዛዙ ጋር ትግል ከማድረግ ፋንታ አርስ በርሳቸው ሲጣላለፉ፣ የራሰቸውንም ድርጅቶች ሲከፋፍሉና ሲሰነጣጥቁ በሚውሉና በሚያድሩበት ሃገር እንዴት አነዚህ ሃይሎች በጋራ በእንድ መሰረታዊ ሃሳብ ዙሪያ ተስማምተው የተባበረ ትግል ማድረግ ይችላሉ። እንዴትሰ ተስማምተው ሁሉም የተስማሙበት የሽግግር መንገስት ያቆማሉ። እንዴትሰ ተስማምተው ሁላችነም በእኩልነት ያስተናግዱናል የሚሏቸውን ተቋማት ማቆም ይችላሉ። ይህ ሃቅ በሆነበት ሃገር እንዴት ይህን ማድረግ እንችላለን ብላችሁ ታስባለቸሁ። ምን ዘዴና ብልሃት አላችሁ።

አቶ አንዳርጋቸው
የተነሱት ጥያቄዎች ከባድና በርካታ ናቸው። እሙን ነው ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚያኮራ ሬኮርድ የላቸውም። ለመጀመሪያ ግዜ የሚያኮራ ስራ ጀምረው የነበረው በ1997 የምርጫ ወቅት ነው። ይህም ቢሆን ህዝቡ ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ የሚል ጠንካራ መልእክት በማስተላለፉ፤ ተነጣጥለው ወደ ምርጫ ቢገቡ እንኳን ድምጽ ሊሰጥ ቀርቶ፣ ትርጉም ለማይኖረው ምርጫ ከቤቱ ወጥቶ የምርጫ ካርድ እንደማይወስድ ግልጽ ካደረገላቸው በኋላ ነበር። እንደምናስታውሰው ህዝብ በስፋት የምርጫ ካርድ ማውጣት የጀመረው ተቃዋሚዎች ተባብረው የመለስን አጋዛዝ ለመግጠም መዘጋጀታቸውን በውል ካወቀ በኋላ ነው። ከእዛ ቧላ ህዘብ በተቃወሚ ፓርቲዎች ላይ ያዘነበትን ሁኔታ ራሳቸው ተቃዋሚዎቹ ፈጥረውለታል። ይህ ማለት ግን በህዝብ በኩል ያለው የለውጥ ፍላጎት ሞቷል ማለት አይደለም።
እንዲያውም ከእዚህ ምርጫ በኋላ በህይወቱ ውስጥ የገጠሙት ፈተናዎች የበለጠ ለለውጥ የሚያነሳሱት ሆነዋል። እዚህ ላይ መረሳት የሌለበት ነጥብ አለ። በዋንኛነት ጥፋቱና ድክመቱ የተቃወሚ ድርጅቶች ቢሆንም፤ በስልጣን ላይ ያለውም መንግስት ያሰፈነው አፈና፣ ህገ ወጥ ድርጉት የራሱ አስተዋጽኦ አድርጓል። በዋንኛነት የፖለቲካ ድርጅቶቹን አበላትና ደጋፊዎች፣ ሆነ የህዝቡን በነጻነት የመሰብሰብ በነጻ ሃሳብ የማቅረብ መብት አገዛዙ በማፈን፣ በራሱ በአገዛዙ ላይ ህዝብ የሚያሰማውን ተቃውሞ መከልከል ብቻ ሳይሆን የተቃወሚ ድርጅቶችና አባላትም እንዚህን የተቃወሚ ድርጅቶች የሚደግፈው ህብረተሰብ በየድርጀቶቹ ውስጥ የሚበቅሉትን ከፋፋዮች አጥፊዎች፣ ተው ሊላቸው ሊቆጣቸው ሊያርማቸው የሚችልበትን መብት ጭምር ነው የመለስ አገዛዝ ያፈነው። አፈና ባለበት ሃገር ሰልጣን ላይ ያለው አገዘዝ ብቻ አይደለም ያለምንም ይሉኝታና ፍራቻ የፈለገውን በደል በህዝብ ላይ መፈጸም የሚችለው ። በየተቃዋሚ ፓርቲ ውስጥ ያለውም እራሱን ከህዝብና ከሃገር በላይ አድርጎ የሚያይም ነውረኛ ሁሉ ነው።

ጋዜጠኛ
አቶ አንዳርጋቸው ይቅርታ ያድረጉልኛና ይህ የአፈና ሁኔታ አሁንም እንደለ ነው። የተቃወሚ ድርጀቶች አሁንም እንደሻቸው ቢሆኑ፣ ህዝብ በሚጎዳ አቅጣጫ ቢጓዙ አሁንም ህዝብ ተው ሊል የሚችልበት አድል የለውም። ነጻነቱ እንደታፈነ ነው። የተቀየረ ነገር የለም። ጥያቄው በእዚህ ሁኔታ ተቃዋሚዎችን በተባለው አላማ ስር የማሰባበቡን ፈተና እምዴት ታልፉታላችሁ ነው።

አቶ አንዳርጋቸው
ቁም ነገሩ ግንቦት7 ይዞት የተነሳው አላማ በዋንኛነት ይደገፋል ብለን ያስፈጽማል የምናምነው ህዝብ ነው። ሁሉንም ፓርቲዎች የሚደግፈው አአባልና ደጋፊ ነው ብለን እናምናለን። ከድርጅቶች ጋር ግንኙነት የሌለውም ዜጋ ይደግፈዋል ብለን እናምናለን። የወገናቸውን መታፍን የሃገራቸውን መዋረድ፣ ያራሰቸው አደርገው የሚያዩ በሰውነታቸውና በዜግነታቸው የመለስን አሰፈሪ ሰላዮች ሳይፈሩ በነጻነት መኖር የሚፈግጉትንም የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች ጭምር ነጻነትን የመንከባከቡ ነጻ ተቋማት እንዲፈጠሩ የሚመኙት ነው የሚል እምነት አለን። የቤተ ምነግስቱ ጠባቂዎች በምርጫ 97 አብዛኛዎቹ ለቅንጅተ ድምጻቸውን መስጠታቸው በመራገጡ በግምገማ መመንጠራቸውን አትርሳ አስፈጻሚው መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ነው ማለት ትችላለህ።

አየህ።በፖለቲካ ታሪካችን ከግንቦት 1997 ምርጫ በፊት በነበሩት ጥቂት ወራት ተፈጥሮ የነበረው የነጻነት መንፈስ፣ የአገዛዙ ባላስልጣናት በሬድዮና በቴሌቪዝን ያደረጉት ክርክር፤ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በተወሰነ ነጻነት በየከተማውና በየገጠሩ ከህዝብ ጋር ያደረጉት ወይይትና ያካሄዱት ቅስቀሳ፣ የገዥ ፓርቲውም የሚያሸንፍ መስሎት በራሱ የመገኛኛ ብዙሃን ስለምርጫና ስለዴመክራሲ አስፈላጊነት ህዝብ የስልጣን ምንጭ ስለሞሆኑ ያካሄደው ቀላል የማይባል ፕሮፓጋንዳ፣ ከምርጫው በፊት በከተሞች የተደረጉ ታላላቅ የዴሞክራሲኛ የነጻነት ትእይንተ ህዝቦች በግንቦት ሰባት የምርጫ እለት ህዘቡ ያሰየው ስነስርአት አዋቂነት ሁሉም በአንድ ላይ ተደምረው በሃገራችን የፖለቲካ ታሪክ ህዘብ የስልጣን ምንጭ ለመሆኑ ለመጀመሪያ ግዜ ከፍተኛ ግንዛቤ እንዲይዝ የተደረገበት ወቅት ነው። ዛሬ ይህንን ግንዛቤ ከህዝብ አይምሮ ውስጥ መፋቅ አይቻልም። ጠመንጃም ይዘህ አስገድደህ ልተገዛው አትችልም አንኳን አንደቀድሞው በማስፈራረሪያ ብቻ። የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ዋንኛው የአለማው ማሳኪያ ጉልበት እውቀት ሃብት ያለው በእዚህ ህዝብ እጅ ነው ብሎ ያምናል።

ለህዝብ እኛ የምንለው ማንም ግለሰብና ሆነ ድርጅት አንተ በነጻነት፣ በፈቃድህ በምረጫ ውክልና ሳትሰጠው በአንተ ስም ስልጣን መያዝ እንደማይገባው ታውቃለህ። እኛም የምንለው ይህንኑ ነው። አንተም እኛም የምንለው በ97 ምርጫ በነጻነት የሰጠኸው ድምጽ ለምን እንደተጭበረበረ ታውቃህ ። የመረጥካቸው ተወካዮችህ የምርጫውን መጭበርበር አስመልክት ለመርጫ ቦርድ አቤት ቢሉ ያገኙትን ምላሽ ታውቃለህ፤ ለፍረድ በቶች አቤት ቢሉ የትም እንዳልደረሱ ታውቃለህ። ምርጫ ቦርዱ ፍርድ ቤቱም የመለስን የስልጣን አድሜ ለማራዘም የቆሙ በአምሳሉ ጠፍጥፎ የሰራቸው በመሆናቸው ፍትህ ልታገኝ አልቻልክም። የመረጥካቸው ተወካዮች የህዝብ ደምጽ አናሰርቅም፤ የምትሰርቁም ከሆነ ይህ ሌብነታችሁ ከእዚህ በኋላ እንዳይደገም ይህንን ሌብነት እንዳላየን አድርገን ለግዜው እንለፍላቸሁ። ይሁንና ተመሳሳይነት ያለው ሌብነት ወደፊት እንዳትደግሙ ዋስትና የሚሆኑንን ሌብነት የሚቆጣጠሩ ማጭበርበር የሚከለክሉ፣ ነጻ የምርጫ ቦርድና የፍትህ ተቋም የመገኛኛ ብዙሃን ይፈጠሩ ባሉ አንተንም ለአዚህ ታገል ብለው ጥሪ ስላቀረቡ በእነሱም ባንተምም ላይ የደረሰውን ታውቃለህ። ለወደፊቱ ምርጫ በነጻነት ለምምረጥ የምችልበትን፣ ሳይጭበርበር ድምጼ የሚቆጠርበትን የኔን የምርጫ ውሳኔ የመጨረሻው መመሪያቸው አድርገው የሚያስፈጽሙ የምረጫ ቦርድ፣ ፍርድ ቤቶች የመላከያና የፖሊስ ሃይል ይመስረቱ ብለህ ላቀረብከው ጥያቄ ተገድለሃል ተቀጥቅጠሃል ተፈናቅለሃል፤ ተሰደሃል ነው የምነለው። እኛም የቆምነው ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ ከተገዥነት ወደ ዜግነት የሚወስድህን በፈቃድህ በምርጫህ የምታቆመውን መንገስት እውን ማድረግ የሚችሉ ተቋማት በቅድሚያ ይመስረቱ ነው የምንለው እንለዋለን።

የፖለቲካ ድርጅቶች ቢሆኑ ሌላው ቢቀር ህዝብ የሰልጣን ባለቤት ሊያድረጉ በሚችሉ በነጻ በሚደራጁ ተቋማት ዙሪያ በጋራ የመስራት ጥያቄ ተቃውመው በህዝብ ውስጥ ተቀባይነት አግኝተው አንደፖለቲካ ድርጅት ለመቀጠል አይችሉም ባይ ነን።ሌላው የሚየስተባብረን ግፊት ራሳቸው ተቃዋሚ ድርጅቶች ያሉበት አስቸጋሪ ሁኔታ ይመስለኛል። ፓርቲዎቹ ራሳቸው ምርጫ የላቸውም። ሁሉም ተቃወሚ ድርጅቶች፣ ከጥቂት በግሰብ ደረጃ ከሚቆጠሩ የመለስ ምንደኞች በስተቀር፣ ሁሉም በመለስ አገዛዝ እብሪት ያልተዋረደ አባለቱ ያልሞቱበት፣በግፍ ያልታሰሩበት፤ በድርጅቱ ህልውና በስሙ በአርማው ላይ ሳይቀር ጥቃት ያልተፈጸመበት ድርጅት የለም። የየነጻ ተቋማት ምስረታ ጥያቄ ለእነዚህ ድርጅቶች የህልውና የክብር ጥያቄ ነው። ያቀረብነውን ሃሰብ ሲቃወሙት አይታየኝም።

ጠምንጃ አንስተው በየበረሃው የሚዋደቁትም ጠመንጃ ሳይኖራቸው ህጋዊ ባለሆነ መንገድ የሚንቀሳቀሱትንም ጨምሮ ማለቴ ነው።ግነቦት7 እያቀረበ ያለውን ከምርጫ በፊት ህዝብን በእውን የስልጣን ባለቤት ማድረግ የሚቻልበትን ሁኔታ ነጻ ተቋመቱን በመፍጠር እናመቻች ለሚለው አቋማች ሰፊ ድጋፍ ከእነዚህ ድረጅቶች እያገኝን ነው። በእዚህ ላይ ደግሞ በላፉት 3 አመታት የእነዚህ ተቋማት አስፈላጊነት ተረድቶ ከፍተኛ ትግል ያደረገው በውጭ ሃገራት የሚገኘው ሃግ ወዳድ ኢትዮጵያዊ በሙሉ ልቡ የሚደግፈው አጀንዳ ነው። ህዝብ የስልጣን ባለቤት ሆኖ ከማየት ሌላ ምንም ሌላ ፍላጎት የሌለው ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ በእዚህ ጉዳይ ላይ የተለያዩ ተቃዋሚ ደርጅቶች በአንድነት ተባበበርው ተግተው እንዲሰሩ ማሳደር የሚችለው ተጽእኖ ቀላል አንዳልሆነ መረዳት ይገባናል።ይህ ማለት ትብብሩን ለማምጣት ቀላል ነው ማለቴ አይደለም። እንደ ዘንደሮ ግን የተሻለ ሁኔታ ገጥሞን አያውቅም ማለቴ ነው። በጋራ መታገል ይቻላል ብልን እናስባለን። ይቻላልም። ከሁሉም ነገር ባለይ ለአድመጮች ለመስረዳት የምነፈልገው ግነቦት ሰባት ያነሳው አጀንዳ ግንቦት ሰባትን ለብቻው ለይቶ የሚጠቅም አንዳችም ነገር በውስጡ የለውም ። ለሁሉም ተቃዋሚ ፓርቲወች ለኢትዮጵያ ህዝብ በመሉ የሚጠቅም ነው። ለመቃወምም አስቸጋሪ የሚያደርገው ይህ ተፈጥሮው ነው።

ጋዜጠኛ
እሺ ባሏቸው ምክንያቶች ተገፋፍተው ሁሉም ተቃዋሚዎች በጋረ ለመስራት ወይም የተባለውን የነጻ ተቋማት ጥያቄ ጥያቄያቸው አድርገው ለመቆም ተስማሙ ልበል። እኔም የማስተባበሩ ስራ አስቸጋሪ እንጂ አይቻልም አልልም። እንደተባለው ተቃዋሚዎች በሙሉ ተስማምተው በጋራ አንድ አይነት አቋም ወሰዱ እንበል፤ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት እንደተለመደው ጥያቂያችሁ ህገወጥ ነው። በህገ መንግስቱ የተቋቋሙ ነጻ ተቋማት ነጻ አይደሉም እያላችሁ፤ ህገ መንግስቱን ለመናድ፣ ሰለምና መረጋጋት ለማናገት እየጣራችሁ ነው። ሰብሰቤ አጉራችኋለሁ ምን ትሆናላችሁ ቢል የት ይደረሳል።

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ቃለ ምልልስ ከገጽ 3 የዞረ

አቶ አንዳርጋቸው

መለስ ዜናዊማ አጉራችኋለሁ ከሚል ማስፈራራት አልፎ ይህንን ጥያቄ ያነሱትን በሽዎች የገደለበት ያጎረበት ከስራቸው ከመኖሪቸው ያፈናቀለበት ለስደት የዳረገበት ሁኔታ ፈጥሯል። ከሁሉ በቅድሚያ መታወቅ ያለበት ህዝብን የስልጣን ባለቤት የማድረግ ጥያቄና የሰልጣን ባለቤት ለማድርግ የሚያስችሉትን ተቋማት የመመስረት ጥያቄ የመለስን አምባገነናዊ ይሁንታ የሚጠይቁ አይደሉም ይህ አምባገነናዊ አገዛዝ ጉሮሮውን ታንቆ ሲገደድ፤ እዛ ከተደረሰ ደግሞ ነፍሴ አውጪኝ ብሎ የዘረፈውን ሃበት ለመብላት ይሮጥ ካለሆነ በስተቀር! ከሰስልጣኑና ከጥቅሙ የሚነቅለውን ነጻ ምርጫ በሃገሪቱ የሚያኪያሂዱ ተቋማት እንዲመሰረቱ ያደርጋል የሚል እምነት የለንም። መለስና ጓደኞቹ በምርጫ 97 የተማሩት ነገር ቢኖር ህዝብ በነጻነት ምርጫ ቢያደርግ እንኳን የመለስ ጀሌዎች ቀርተው እራሱ መለስ ዜናዊም በተወለደበት በአድዋም እንደማይመረጥ ነው። በተወለድንበት ወይም ህዝብ በሚያውቀን መንደር እንመረጣለን ብለው የገጠሩ ህዝብ ይደግፈናል ከሚል ቅዠት ከከተማ ወጥተው በገጠር የተወዳደሩ የአገዛዙ ቱባ ባለስልጣናት እነ በረከት ሰመኦን አካካሱ ኢላላ እነ አባዱላ ገማዳ አንጁነዲን ሰዶ በአርሶ አደሩ ምን ያህል እንደተተፉ በምረጫው አይተውታል። የመለስ አገዛዝ በምንም አይነትና ሁኔታ ከምርጫ 97 በፊት ከሰራቸው ጸረ ሃገርና ጸረ ህዝብ ድርጊቶች በተጨማሪ ከምርጫ 97 በኋላ ያካሄደውን ተጨማሪ ሃገር የመሸጥ. ህዝብ የፍጅት፣ የግድያ፣ የአፈናና የዘረፋ ወንጀል ተጨምሮበት ራሱን ለሌላ ነጻ ምርጫ ፈቃደኛ ደርጋል ብሎ የሚያስብ ካለ አውቆ የተኛ ብቻ መሆን አለበት።ስለሆነም ንቅናቄያችን የሚለው የሃገራችን ተቃዋሚዎች በሙሉ በእዚህ አገዛዝ መሰራተዊ ባህርይ ላይ ግልጽ የሆነ አቋም በቅድሚያ ሊይዙ ይገባል። ይህ አገዛዝ ፍጹም አምባገነናዊ ብቻ ሳሆን ጸረ- ኢትዮጵያ አገዛዝ ነው። ይህንን ሃይል በልመና በሽምግልና፣ በሽወዳ በሸንገላ በሌሎችም ዘዴዎች ዴሞክራሲያዊ ሃገር ለመገንባት ፈቃደኛ ሆኖ ከተቃዋሚዎች ጋር በአንድ ወንብረ ተቀምጦ ይደራደራል የሚል ቅዠት ሊኖራቸው አይገባም ነው።

ስለሆነም ተቃዋሚዎች በሙሉ ስለነጻ ምርጫ ወይም ለነጻ ምርጫ መኖር አስፈላጊ የሆኑ ተቋማት ጥያቄ እናነሳለን ቢሉ በነመለስ እንደማይደመጡ፣ ጉዳዩን ወደ ህዝብ እንወስዳለን ቢሉ የመለስ አገዛዝ እንደማይፈቅድ፣ ያለእርሱ ፈቃድ እናደርገዋለን ቢሉ ድርጅቶችን ህገወጥ ለማድረግ መሪወቻቸውን ደጋፊዎቻውን ለመግደል ለማሰር የማይመለስ መሆኑን በቅድሚያ ማወቅ አለባቸው። ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ለዴሞክራሲና ለነጻነት የሚደረግ ትግል እንዲህ አይነት አስፈሪ መዘዝ እንደሚኖረው በቅድሚያ መታወቅ አለበት። ስለዚህም ተቃዋሚዎች መለስ በቀላሉ እንዳያስፈራራቸው በተናጠል እንዳይመታቸው፣ በጋራ በተስማሙበት ጉዳይ ላይ አንድነታቸውን አጥብቀው መቆም አለባቸው። በጋራ ሆነው ህዘብም በጋራ ደግፏቸው እንዲቆም ጥሪ ማቅረብ አለባቸው።

ከማንኛውም ነገር በላይ የመለስን መንግስት ጨፍጫፊነት እያወቁ፣ በመለስ አገዛዝ እውቅና አግኝተው በይፋ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶች ህዘብን የስልጣን ባለቤት የሜያደርጉ መሰረታዊ ጥያቄዎች ቢያነሱ ሊደርስባቸው የሚችለውን አበሳ አስቀድመው ያወቁ ሊሆኑ ይገባል ብልን እናስባለን።ግንቦት ሰባት ይህንን የመለስ ዜናዊን አገዛዝ መሰረታዊ ባህርይ ግምት ውስጥ አስገብቶ አቋም ወስዷል። ይህ አገዛዝ በኢትየጵያችን ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመገንባት የኢትዮጵያ ህዝብ ለሚያደርገው ጥረት ደንቃራ ነው በለን እናምናለን። በተለይ ከምርጫ 97 በኋላ እንዚህ እብሪተኞች በማንአለብኝነት የፈጸሙትን ወንጀል ካየን በኋላ እርማችንን አውጥተናል።

አልፎ አልፎ የዴሞክራሲያዊ ተቋማት ግንባታው አገዛዙን ጨምሮ ሊካሄድ ይችላል የሚል ንግግር በመናገራችን አድማጮቻችን ግራ መጋበት የለባቸውም። ይህንን የምንለው በጋራ የሃገሪቱን ችግር ለመፍታት የሚያስችለውን በር የዘጉት ለስልጣን ሟች የሆኑት መለስና ጀሌዎቹ እንጂ እኛ እንዳልሆን ለማሳየት ብቻ ነው። በተረፈ እነዚህ ጉደኞች ህላችንም በጋራ ስለሃገር መምከር ወደምንችለበት መድረክ ይመጣሉ የሚል ተስፋ ወይም ቅዘት የለንም። ግንቦት 7 በፕሮግራሙ ያስቀመጣቸውን ህዘብን የስልጣንነ ባለቤት የሚያደርጉ ጉዳዮች አንግቦ ለመታግል የመለሰን ቡራኬና መልካም ፈቃድ አይጠይቅም። አላማችንን ለማሳከት አስፈላጊ የሆነውን አደረጃጀት የትግል ስልትና መታገያ ዘዴ ቀይሰናል። የድርጅቱን መሪዎች አበላትና ደጋፊዎች መለስ ዜናዊ በቀላሉ ሰብስቦ ሊያጉር የማይችልበትን የአደረጃጅ ስልት ቀይሰናል።

በይፋ በአደባባይ አበላቶቻን ና ደጋፊዎቻችን ለመለስ ሰላዮች ታውቅው ለጥቃት እንዲጋለጡ አናደርግም። ሚስጥራዊ የድብቅ አደረጃጀት ብቻ እንደሆነ ከመለስ አብሪት መከላከያው አውቀናል። እንዲህ አይነቱን አደረጃጀት በንድፈ-ሃሳብ ደረጃ መቅረጽ ሆነ በተግባር በስራ ላይ ማዋል የሚስችል ብቃት እንዳለን መለስ ዜናዊም እራሱም ያውቀዋል። በእዚህ መንገድ ሄደን ለራሱ የስልጣን ባለቤትንት ለራሱ መብት መታግል የሚፈልገውን፣ በሃገሩ ላይ የሚካሄደውን በደል፤ አንድነቱን የሚያናጋ ዘረኝ ከፋፋይነት ለማስቆም የሚፈልገውን፤ ጥቂቶች የሃገሩን ሃብት እየዘረፉ የሚቀናጡበትን ሚሊዮኖች በረሃብ የሚያልቁበትን የጥቂት ሆዳሞች አገዛዝ ለማስቆም የሚፈልገውን በሚሊዮኞች የሚቆጠር ህዝብ በቀላሉ በፍጥነት ለማደራጀት እንችላለን። ይህንን ስራ ጀምረናል። የእዚህን አደረጃጀት ጥንካሬ በየግዜው እንደ ሁኔታው በመገምገም ንቅናቄያችን ለሚያኪሂደው ማናቸውም አይነት ትግል የጀርባ አጥንት እናደርገዋለን። በእዚህ አደረጃጀትአማካይነት በተለያዩ የህዝባዊ እምቢተኛነት የትግል ስልቶች ይህ አገዛዝ እየዘረፈና እየገደለ ሃገር እየሸጠ ተደላድሎ እንዳይገዛ ትልቅ የነጻነትና የሃጋር ባለቤትነት ንቅናቄ መገንባት እንችላለን ብለን እናምናለን። ከእዚህ በተጫመሪ ይህ እብሪተኛ አገዛዝ የሚተማመነው በጉልበቱ እንደሆነ ስለምናውቅ። ልንቀሰቅሰው የምንችለውን በህቡእ የተደራጀ ህዝባዊ የእምቢተኛነት ትግል እነመለስና እነበረከት በጅምላ አስራትና በጅምላ ግድያ እንወጣዋለን የት ይረደርሳሉ በሚል እብሪት ተወጥረው እንደሚኖሩ እናውቃለን።ለእዚህ ቢሆን ወገንም ሆነ ጠላት በግልጽ እንዲያውቃው የምንፈልግው፣ ግንቦት 7 ንቅናቄ መለስ ነፍሰ -ገዳይ ጉዋደኞቹ በማንአለብኝነት የወገኖቻችን ደም እያፈሰሱ ከእዚህ በኋላ እጃችንን አጣጥፍን እንደማንቀመጥ ። በግንቦት 7 ውስጥ የተሰባሰብነው ግለሰቦች አብዛኞቻችን ሳንወድ በመለስ ጥጋብና እብሪት ተገፍተን ህጋዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ወገናችንን ለማደራጀት ለማንቀሳቀስ፤ለመብታችን ለሃገር ባለቤትነታችን በጋራ ለመታገል፣ በዜግነታችን የሚገባንን መብቶች በመገፈፋችን፣ ከአገዛዝ ስርአቱ ፈቃድና እውቅና ውጭ ትግል ለማድረግ የተገደድነው።

ንቅናቄያችንን ደግፎ የሚቆመውን አባለትና ህዝብ ከመለስ ጥቃት መከላከል አስፈላጊ እንደሆን አንውቃለን። ይህንን የመከላከያ አቅም እናዳራጃለን አስፈላጊና ተገቢ ነው ብለን ባመንነው ሰአትና ወቅት እንደአስፈላጊነቱ በስራ ላይ እናውላልን። ከእዚህ በተጨማሪ መለስ የሃገር ባለቤትነታቸውን የዜግነት መብታቸውን ገፎ ኑሯቸውን በዱር በገደሉ እንዲየደርጉ ካደረጋቸውን ጠመንጃ አንስተው የሚንቀሳቀሱ ሃይሎች ጋር ተባብረን እንሰራለን። እነዚህ ሃይሎች ህዘብን የስልጣን ባለቤት ለማድረግ ግንቦት 7 ባስቀመጣቸውን መሰረታዊ ጉዳዮችና ትግላቸው የኢትዮጵያን አንድነት ጠብቆ የሚሄድ እስከሆነ ድረስ ምንም ልዩነት አይኖረንም። በእዚህም ከሁሉም ሃይሎች ጋር በከፍተኛ ፍጥነት እተቀራረብን እና እተስማማን ነው። በእዘህ ፈርጅ የምናደርገው ጥረት መለስ ዜናዊ እንደሚያስበው በጠመንጃ ብዛት ሀገርና ህዝብ እየገድልኩ እቀጥላለሁ የሚል ህልሙ በአጭር ግዜ ውስጥ ወደ አስፈሪ ቅዠት መቀየር እንችላላን ብለን እናምናለን።

በአጠቃላይ በመለስ አገዛዝ እውቅና አግኝተው የሚንቀሳሰቀሱ ድርጅቶች በአንድነት፣ እስካሁን ስገልጸው በነበረው ህዝባዊ አጀንዳ ዙሪያ ከተሰባሰቡ፤ በሌላ በኩልም የመለስ አገዛዝ እውቅና ሳያስፈልጋቸው በድብቅና በሚሰጥር ተደራጅተው የሚንቀሳቀሱ ሃይሎች በአንድነት ከህዝብ ጋር ተሳስረው ከቆሙ ቀደም ብለህ ያነሳኸውን የመለስን ማስፈራሪያና ማስፈራራውን ማስፈጸሚያ ጉልበቱን ማምከን አያስቸግርም።

ጋዜጠኛ

አንዳንድ ግለሰቦችና ድርጅቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲ ለማስፈን የተጀመረው ትግል ህጋዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ መቀጠል ይችላል፤ ግንቦት 7 ይህንን አገዛዝ በአመጽ ጭምር እንግጠመው በማለት ሃገሪቱን የከፋ ቀውስ ውስጥ ሊጨምራት ይችላል ይላሉ። በተለይ እርሰዎም ይሁን ዶ/ብርሃኑ ሌሎችም ዛሬ በግነቦት 7 ውስጥ የነበራችሁ ግለሰቦች በአንድ ወቅት ከሰላማዊ ትግል ሌላ ምንም አማራጭ ሊኖር አይችልም ሲል የነበረ ድርጅት አባለት ነበራችሁ፣ አንዳንዶቻችሁ በተለይ ዶ/ር ብርሃኑ ሰላማዊ የትግል ስልት አማራች የሌለው ለመሆኑ የተናገሯቸው ንግግሮች በድምጽና በምስል ቀርጸው በማስረጃነት ሲያቀርቡ ይታያሉ። እንዴት ከእንዲህ አይነቱ የቆየ አቋም አመጽን ለመጠቀም እቅድ ያለው ድርጅት መስራቾች ሆናችሁ። አሁንም በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ መታገል ይቻላል ለሚሉት ምን መልስ አላችሁ።

የመጨረሻውን ክፍል በሚቀጥለው ሳምንት ይጠብቁ


## ውድ አንባቢዎች

ግንቦት7 ንቅናቄ በሳምንት ሶስት ግዜ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሃሙስና ቅዳሜ ለኢትዮጵያና በአካባቢው ለሚገኙ ሃገሮች የሬድዮ ስርጭት መጀመሩን ያውቃሉ። ካለወቁ እነሆ!!

**ከምሽቱ 2.00 እስከ 2.30**

**በአጭር ሞገድ**

**በ17655 ኪሎ ኽርዝ**

**በ16 ሜትር ባንድ**

**ወይም**

**በ21555 ኪሎ ኽርዝ**

**በ13 ሜትር ባንድ**

**ይከታተሉ!!**

**ላልሰማ ያሰሙ!!**

**በያላችሁበት መረጃ በማሰባሰብ ጎጠኛውና አምባገነኑ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በህዝባችንና በሃገራችን ላይ የሚፈጽመውን ወንጀል ያጋልጡ!! የሬድዮ ስርጭታችን፣ ያማረና የተዋጣላት እንዲሆን በእውቀት፣ በምክርና በገንዘብ ድጋፍዎን ይለግሱን።**

**መረጃ ሃይል ነው!! ህዝባችንን በመረጃ እናስታጥቀው!!**